# እንዴት

## ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ላይ ጥናትና ምርምር በሚከናወንበት ጊዜ ቋንቋን እንዴት ግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚቻል

ለ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና በሰብአዊነት ወይም በልማት ስራ ሁኔታዎች ውስጥ ላሉ ተመራማሪዎች

### ቋንቋ ለምንድን ነው አስፈላጊ የሆነው?

- ቋንቋ የማንኛውም ምርምር ወይም ክትትል እና ግምገማ ሥራ አስፈላጊ አካል ነው፣ ነገር ግን በተለይ እንደ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ያሉ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው እና ሥርዓተ-ፆታ ነክ ርእሶች ላይ ለሚደረግ ምርምር በጣም ወሳኝ ነው።
- በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ስለ ወሲብ እና ጥቃት ለመነጋገር የምንጠቀምባቸው ቃላት በፆታ መካከል፣ በእድሜ እና በማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ቡድኖች መካከል እና እንደምናነጋግረው ሰው ይለያያሉ።
- ተመራማሪዎች ለእንደዚህ አይነት ልዩነቶች ካልተዘጋጁ እና ትኩረት ካልሰጡ በስተቀር ስለሰዎች ልምዶች፣ ፍላጎቶች እና ምኞቶች ጠቃሚ መረጃ ሊያመልጣቸው ይችላሉ።

ይህ አጭር መመሪያ ተመራማሪዎች እና የፕሮግራም ሰራተኞች በወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ምርምር እና ክትትል ውስጥ የቋንቋ መሰናክሎችን ለማሸነፍ ሊወስዷቸው የሚችሉ ተግባራዊ እርምጃዎችን ይጠቁማል።



### ምን አይነት ስህተቶች ሊፈጸሙ እንደሚችሉ እና እንዴት አለመፈጸማቸውን ማረጋገጥ እንደሚቻል

ተግባቦት ላይ ችግር ሊያጋጥም ይችላል

- ጥናቱ የሚካሄደው ተሳታፊዎች ሙሉ በሙሉ በማይረዱት ወይም በማይመቻቸው፣ ወይም ተዛማጅ ልምድ እና ግንዛቤ ያላቸውን ሰዎች በማያካትት **ቋንቋ ወይም ያነጋገር ዘይቤ** ከሆነ
- ተመራማሪው **የሚያገሉ ወይም ክልክል የሆኑ** መልእክቶችን የያዙ ተሳታፊዎች የማይመቿቸውን ቃላት ከተጠቀመ
- ተመራማሪው ተሳታፊዎች የማይረዷቸውን ወይም በተለየ መንገድ የሚረዷቸውን **ቃላት** ከተጠቀመ።

ቢያንስ፣ ተመራማሪዎች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው:

- ✓ ሰዎች የሚናገሩትን ቋንቋ መረዳት
- ✓ በጉዳዩ ላይ ለመወያየት ተሳታፊዎች የሚጠቀሙባቸው ዋና እና ተመራጭ ቃላት እና ጽንሰ-ሐሳቦች ምን እንደሆኑ መረዳት
- ✓ የትኞቹ ቃላት እና ጽንሰ-ሐሳቦች ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው እንደሆኑ እና መተው እንዳለባቸው መረዳት
- ✓ ሰዎች ጥቅም ላይ ስለሚውሉ ቃላት ተመሳሳይ ግንዛቤ አላቸው ብለው አለመገመት።
- ✓ ሁላችሁም ስለ አንድ አይነት ነገር እየተነጋገራችሁ መሆኑን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ቃላቶች እና ጽንሰ-ሐሳቦች ለማብራራት መጀመሪያ

ሳጥን 1 [በባንግላዲሽ ከሚገኙ የሮሂንጊያ ስደተኞች ጋር የተደረገ](#) ጥናት እንደሚያሳየው ሴቶች እና ልጃገረዶች ቢጠቀሙት ተቀባይነት የሚኖረውን ቋንቋ የተመለከቱ ጠንካራ ባህላዊ ልማዶች፣ የእርዳታ ሠራተኞችን የወሲባዊ ጥቃት ጥቆማዎችን ከመረዳት አቅበዋቸዋል። አንዳንድ ቃላቶች ጭራሽ የተከለከሉ ናቸው፤ ስለዚህ ሴቶች እና ልጃገረዶች የተለያዩ የጥቃት ዓይነቶችን ለማመልከት እንደ “መበከል”፣ “ጭቆና” እና “ውርደት” ያሉ ሌሎች ቃላትን

## መርሆች

**ማነጋገር የሚፈልጓቸውን ሰዎች ቋንቋ ይናገሩ**

- በወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ላይ የሚደረግ ጥናት በተለይ ለተገለሉ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች ትኩረት መስጠት አለበት።
- የትኞቹን ቋንቋዎች እንደሚናገሩ ማወቅ፣ ተመሳሳይ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ተመራማሪዎችን መቅጠር እና የምርምር መሳሪያዎችን ወደ እነዚያ ቋንቋዎች መተርጎም ያስፈልግዎታል።
- ማህበረሰቦች ብዙውን ጊዜ በቋንቋ የተለያዩ በመሆናቸው ሁሉም ሰው ብሔራዊውን ወይም ብዙሃኑ የሚናገረውን ቋንቋ አይናገርም ወይም አይረዳም።

**ተሳታፊዎች የሚመቻቿቸውን ቃላት ይጠቀሙ**

- የምንጠቀምባቸው ቃላት ገለልተኛ አይደሉም። የቃላት ምርጫችን በማህበራዊ እና ባህላዊ ደንቦች ይመራል።
- እነዚህ ደንቦች ስለሚለያዩ፣ አንድ ቃል ለተለያዩ ሰዎች የተለየ ትርጉም ሊኖረው ይችላል።
- አንዳንድ ቃላት የሚለጿቸውን ሰዎች ወይም ድርጊቶች በተመለከተ አስቀድሞ ድምዳሜ/ፍርድ ላይ የተደረሰ የሚያስመስል አንድምታ ይኖራቸዋል። አንዳንዶቹ ቃላት አጸያፊ እንደሆኑ ይታያሉ ወይም ሴቶችን ወይም ልጆችን የመሳሰሉ የተወሰኑ ቡድኖች ሊጠቀሟቸው የማይችሉ ተደርገው ይታያሉ። አንዳንዶቹ በተወሰኑ ቡድኖች ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ እና የእነዚያን ቡድኖች አባልነት የሚያመለክቱ ናቸው።

**ለሁሉም ሰው ተመሳሳይ ትርጉም የሚሰጡ ቃላት ተጠቀም**

- ስለወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መነጋገር አስቸጋሪ ሊሆን ስለሚችል፡ ተዘዋዋሪ ወይም የህክምና ቃላትና ምህጻረ ቃላት የመሳሰሉቴክኒካል ቃላትን ወይም የውጪ ቋንቋዎች ቃላትን ተጠቅመን ብዙ ጊዜ ራሳችንን ከእነዚህ ጉዳዮች እናርቃለን።
- ሁሉም ሰው እነዚያን ቃላት በተመሳሳይ መንገድ ይጠቀማል ወይም ይገነዘባል ብሎ ማሰብ አደገኛ ነው። ስለዚህ በተለይ በወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ምርምር ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉትን ቃላት ትርጉም ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው።

## ትክክለኛውን ቋንቋ መጠቀማችንን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል

### 1. ሰዎች የትኛውን ቋንቋ ይናገራሉ?

- ሰዎች የትኞቹን ቋንቋዎች እንደሚናገሩ ይወቁ። በዚህ ላይ የማህበረሰብ አባላት (የማህበረሰብ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ) ምርጥ የመረጃ ምንጭ ናቸው። ድምፃቸው ሁል ጊዜ የማይሰማውን ሰዎች ምርጫዎች በትክክል ለማወቅ በሰፊው ማማከርዎን ያረጋግጡ። ለመረጃ ምንጮች ከዚህ በታች ያለውን ሳጥን 2 ይመልከቱ።
- ሰዎች በሚናገሩትን ቋንቋ በተመለከተ ምክክር በሚኪያሂዱበት ጊዜ አካል ጉዳተኞችን ያካትቱ እና ለምርምርዎ ተገቢ የሆኑ የግንኙነት ዘዴዎች ላይ ያላቸውን አስተያየት ይጠይቁ። እነዚህም የምልክት ቋንቋ መተርጎምን፣ የተዘጉ መግለጫ ፅሁፎችን እና በፅሁፍ ላይ ከተመሰረቱ የምርምር መሳሪያዎች ይልቅ የእይታ አጠቃቀምን ሊያካትቱ ይችላሉ። እነዚህ ጉዳዮች ግምት ውስጥ ባልገቡበት ሁኔታ የእነርሱ ግንዛቤ እና ከጥቃት ጥበቃ እና ከ ወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጋር የተያያዙ ልምዶቻቸው የመስማት ዕድላቸው አነስተኛ ነው።
- የምንናገርበት መንገድ እና የምንጠቀምባቸው ቃላቶች እና ቋንቋዎች ማንነታችንን የምናረጋግጥበት መንገድ አካል መሆናቸውን ልብ ይበሉ። በመሆኑም፣ ከሌሎች ሰዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለንን ልዩ ነት ከማመልከታቸውም በላይ መተማመንን እና መተሳሰብን ሊቀንሱ ይችላሉ። በማህበረሰቦች መካከል

የግጭት ወይም የውጥረት ታሪክ ባለበት ሁኔታ ውስጥ፣ “የተሳሳተ” ንግግር ወይም ያነጋገር ዘይቤ ጥሩ ሀሳብ ያለው ግለሰብን እንደ ስጋት ሊያስቆጥረው እና ግልጽ ውይይትን ሊያደናቅፍ ይችላል። ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ጉዳዮች እንደሚያደርጉት በተለይ የምርምር ርዕሱ አይነት ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ከሆነ ወይም የመገለልን ጉዳይ የሚዳስስ ከሆነ ችግር ሊፈጥር ይችላል። ቋንቋው ከጥቃት የተረፉትን የሚደግፍ እና የማይጎዳ መሆኑን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

- ከአካባቢ ሰዎች ጋር በመነጋገር የንግግር ዘይቤያቸው የሚገባ እና ተቀባይነት እንዳለው በማረጋገጥ የምርምሩ ተሳታፊዎች የሚመርጡትን ቋንቋ የሚናገሩ ተመራማሪዎችን ይቅጠሩ። ይህም ተሳታፊዎች በጎረቤት ወይም በቤተሰብ አባል በኩል ምላሻቸውን ከማስተላለፍ ይልቅ ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ እና በተረጋጋ ሁኔታ ስሱ ስለሆኑ ጉዳዮች እንዲናገሩ ያስችላቸዋል[1]።
- የፕሮግራሙ ሰራተኞች በቀላሉ ሊጠይቋቸው የማይችሏቸውን ጥያቄዎች ለመጠየቅ በምርምር ቡድኑ ውስጥ “ውጫዊ ሰው” መኖሩ ጠቃሚ መሆኑን አስቡበት። ይህም በአካባቢው ያሉ የእርዳታ ሰራተኞች በወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት ወይም ወሲባዊ ትንኮሳ ጥፋተኛ እንዳልሆኑ፣ ወይም ተሳታፊዎች ከፕሮግራሙ ሰራተኞች ጋር ለመወያየት የማይፈልጉትን ርዕሰ ጉዳይ አንስቶ በመጠየቅ ተሳታፊዎች መጀመሪያ ላይ የሰጣቸውን ሃሳቦች መገዳደርን ሊያካትት ይችላል።
- የምርምር ቡድንዎን የቋንቋ ጉዳዮችን በተመለከተ ንቁ እንዲሆኑ እንዲሁም የምርምር መሰሪያዎችን እነሱ ለማንበብ እና ቃለ መጠይቅ ለማድረግ የበለጠ ወደሚያመቻቸው ቋንቋ ወይም ቋንቋዎች

**ሳጥን 2 ሰዎች የሚናገሩት የትኛውን ቋንቋ እንደሆነ ማወቅ**

ቁጥራቸው እየጨመረ ላሉ አገሮች የቋንቋ መዘርዝሮችን እና የቋንቋ መረጃ በነፃ ከዚህ ያውርዱ https://translatorswithoutborders.org/language-data/. ይህ አካባቢያዊ ዝርዝሮችን አይሰጥም፣ ነገር ግን ሰዎችን ስለ ቋንቋ ምርጫዎች ለመጠየቅ የሚያስፈልጉትን የቋንቋ ችሎታዎች ለመለየት መነሻ ሊሆን ይችላል። ከተቻለ አራት መደበኛ ጥያቄዎችን በታቀዱ የፍላጎት ግምገማዎች እንዲተረጉሙ ያሰልጥናቸው። (ከዚህ በታች ይመልከቱ)

## 2. የትኞቹን ቃላት መጠቀም አለብን?

ጥናቱን በሚዘጋጅበት ጊዜ፣ ከተመራማሪው ቡድን ጋር ጊዜ ወስደው በማሰብ ሊኖሩ ስለሚችሉ የግንኙነት እንቅፋቶች ያማክሩ። ከጥናትና ምርምር በፊት በስልጠና ወቅት የቃላቶች እና የቃላት ውይይት ለማረግ ያቅዱ። ሃሳቦቻቸውን ለመሰብሰብ እና ትኩረታቸውን ስሱ ሊሆኑ ወደሚችሉ ጉዳዮች ለመሳብ በስልጠና ወቅት ስሱነት ሊኖራቸው በሚችሉ ቃላት እና ፅንሰ-ሀሳቦች ላይ ከምርምር ረዳቶች ጋር ይነጋገሩ።

- በተመራማሪው ቡድን እና በተሳታፊዎች መካከል በሚደረጉ ውይይቶች ወቅት ሊነሱ የሚችሉ በምርምር መሳሪያዎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ እንዲሁም ከምርምር ርእሱ ጋር የተያያዙ ቃላትን እና ፅንሰ-ሀሳቦችን ዝርዝር ያውጡ።
- እነዚህን ቃልት እና ጽንሰ-ሐሳቦች ከተመራማሪው ቡድን ጋር ተወያዩ ባቸው። የተለያዩ ቡድኖች አግባብነት ባለው ቋንቋ፣ እንደሚያነጋግሩት ሰው እያንዳንዱን ጽንሰ ሃሳብ በተመለከተ ሊጠቀሟቸው የሚችሉትን የተለያዩ አገላለጾች በአንድ ላይ የያዘ ዝርዝር በማዘጋጀት ይጀምሩ። ለምሳሌ እንደ የወር አበባ/ የወር አበባ ጊዜ/ ወርሃዊ ዑደት የመሳሰሉ ቃላትን በምሳሌ ለማስረዳት መጠቀም ይችላሉ።
- ተሳታፊዎች ሊጠቀሙባቸው ወይም ሊመርጧቸው የሚችሉትን ቃላት እና አባባሎች ያስቡ። የትኞቹ ቃላት ወይም ጽንሰ-ሐሳቦች ጥንቃቄ የሚያሻቸው ናቸው? የትኞቹ ቃላት ወይም ጽንሰ-ሐሳቦች በተሳታፊዎች መካከል ሃፍረትን ወይም ቁጣን ይፈጥራሉ? የትኞቹ ቃላት ወይም ጽንሰ-ሐሳቦች መተው አለባቸው? ለነዚህ ሁሉ ቃላት እና ፅንሰ-ሀሳቦች የትኞቹ ትርጉሞች በጣም ትክክለኛ እና በጣም ለመረዳት የሚያመቹ ይሆናሉ? የትኛዎቹ ስያሜዎች ወይም ቃላት ደጋፊ ከባቢን ይፈጥራሉ? ይህ በተለይም ከወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ የተረፉ ወይም ማንኛውም ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ካለው ሰው ሰው ጋር በሚሰራበት ጊዜ በጣም አስፈላጊ ነው።
- የትኞቹ ቃላት በማህበረሰቡ ዘንድ አስጸያፊ ተደርገው የሚታዩ በመሆናቸው ወይም በኋላ ላይ ችግር የሚፈጥሩ በመሆናቸው ምክንያት ለምርምር ረዳቶቹ ለአጠቃቀም አስቸጋሪ እንደሚሆኑ ተወያዩ።

[1] እንደ ወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን የመሳሰሉ ስሱ ርእሰ ጉዳዮችን በተመለከተ ከማህበረሰቡ ውስጥ ተመራማሪን መቅጠር ግላዊነትን አደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችል ያስታውሱ። ግላዊነትን ለመጠበቅ ከማህበረሰቡ ውጪ የሆኑ ተመራማሪዎችን መቅጠርን ቢያስቡበት መልካም ነው።

- ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸውን እና የማይችሏቸውንቃላት ዝርዝር ያዘጋጁ። ከሙከራ በፊት የምርምር መሳሪያዎችን ለማስተካከል ይህንን ይመልከቱ።
- ለተሳታፊዎች መገለጽ ያለባቸውን የቃላት ስያሜ ወይም የቃላት መነሻ ስብስብ ይለዩ። የትኞቹ ቃላት ለተሳታፊዎች አዲስ  በመሆናቸው መተርጎም ያስፈልጋቸዋል?
- የምርምር መሳሪያዎችዎን ሲሞክሩ በቃላት እና ፅንሰ-ሀሳቦች ዙሪያ ጥንቃቄ ሊያስፈልጋቸው ለሚችሉ ጉዳዮች ልዩ ትኩረት ይስጡ። ከሙከራው በተገኘው ግብዓት መሠረት በምርምር መሣሪያዎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉትን የቃላት ስያሜ ለማስተካከል ጊዜ ይውሰዱ እንዲሁም ጥቅም ላይ ለማዋል የበለጠ አግባብነት ያላቸውን ቃላት በተመለከተ ለምርመራ ቡድኑ መግለጫ/ማብራሪያ ይስጡ። (ከዚህ በታች

> አግባብነት ባለው ቋንቋ “መደፈር” የሚለው ቃል አንድ ወንድ በሴት ላይ የሚፈጽመውን ወሲባዊ ጥቃት ለማመልከት ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል እንደሆነ፣ በወንዶችና በወንድ ልጆች ላይ የሚፈጸመውን ጥቃት ለመግለጽ ትክክለኛው ቃል ላይሆን ይችላል። ተሳታፊዎች በወንዶች ላይ ከሚደርስ መደፈር ጋር በይበልጥ ሊያያይዙት የሚችሉትን ለምሳሌ እንደ

ያለውን ሳጥን ይመልከቱ)

## 3. በመረጃ አሰባሰብ ወቅት እነዚህን ቃላት እንዴት ማስተዋወቅ ይቻላል?

- በቃለ-መጠይቆች እና የትኩረት ቡድን ውይይቶች ላይ ለተሳታፊዎች ገላጭ የሆኑ አንዳንድ ቃላትን ሊጠቀሙ እንደሚችሉ እና ይህም ማንንም ለማሸማቀቅ ወይም ለመሳደብ እንዳልሆነ ለተሳታፊዎች ያስረዱ። እነዚህን ቃላት የሚጠቀሙት ጉዳዩን በተሻለ ለመረዳት ሲሉ እንደሆነና በቃለ መጠይቁ ወይም በውይይት ጊዜ ጥቅም ላይ ቢውሉ ለሁሉም ሰው የሚመቹት ቃላት

> አንድ የእርዳታ ሰራተኛ ከተጎጂው ማህበረሰብ አባል ጋር ለስጦታዎች ወይም ለእርዳታ ቅድሚያ ለማግኘት ሲባል ወሲብ ቢፈጽም ተሳታፊዎች እንደ “ወሲባዊ ብዝበዛ” ላይቆጠሩት ይችላሉ። እንደዚያ ከሆነ፣ ሰዎች ያንን ሁኔታ እንዴት እንደሚገልጹት ልትጠይቃቸውና ስለ ጉዳዩ ለመነጋገር ይህን አገላለጽ በመተካት ለመጠቀም መስማማት ትችላለህ።

የትኞቹ እንደሆኑ በስምምነት መወሰን እንደምትችሉ ያብራሩ።

- ተሳታፊዎችን እንዲሰይሙ ከመጠየቅ ይልቅ እራስዎ ስያሜውን ያስተዋውቁ። ተመራማሪው ይህንን ቃል በምርምር እንቅስቃሴው ወቅት ቢጠቀምበት ምቾት እይሰማቸው እንደሆነ ተሳታፊዎችን ይጠይቁ። በምርምር እንቅስቃሴው ወቅት ቃሉን ራሳቸው ለመጠቀም ምቾት ይሰማቸው እንደሆነ ጠይቋቸው። ከእነዚህ ጥያቄዎች ለሁለቱም “አይሆንም” ብለው ከመለሱ፣ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚመርጡት አማራጭ ቃል ካለ ይጠይቋቸው። ተሳታፊዎች ዓይን አፋር ከሆኑ ወይም ሀሳብ ከሌላቸው አማራጭ ስያሜዎችን ለመጠቆም ዝግጁ ይሁኑ።
- “ሥነ ምግባር የጎደለው ተግባር” በሚለው ቃል መጀመር እና ይህ ብዙ ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል ማስረዳት ይችላሉ። የፆታ ብዝበዛን፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ ብዙ አይነት የስነምግባር ጥፋቶች አሉ ይህም ምርምርዎ ለመረዳት ያቀደው ነው። እንደ “ወሲባዊ” ያሉ ቃላት የተከለከሉበት አውድ ውስጥ፣ “ሥነ ምግባር የጎደለው ተግባር” የሚለውን ቃል ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ እንደምትጠቀም ከምርምር ተሳታፊዎች ጋር መስማማት ትችላለህ።
- እነዚህን ቃላቶች ፍሊፕ ቻርቶች ወይም በጥቁር ሰሌዳዎች ላይ ከመጻፍ ተቆጠቡ፣ ይህ የማያቋርጥ የሃፍረት ስሜት ሊያስከትል ይችላል። ሌሎች በምርምር እንቅስቃሴው ውስጥ የማይሳተፉ ሰዎች እነዚህን ቃላት ካዩ አለመግባባትን ወይም ቁጣን ሊያስከትል ይችላል። በምርምር ተሳታፊዎችዎ ላይም ጉዳት ሊያስከትል ይችላል።

## 4. የሁሉም ሰው ግንዛቤ ተመሳሳይ መሆኑን ማረጋገጥ።

- በወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ እና ጾ ታን መሠረት ባደረገ ጥቃት መካከል ያለውን ልዩነት ለተሳታፊዎች እና ለተመራማሪው ቡድን ለማብራራት ጊዜ ይውሰዱ። ወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ብዙውን ጊዜ ለማህበረሰቦች አዲስ ፅንሰ-ሀሳብ በመሆኑ ሰዎች ስለ ጾ ታን መሠረት ስላደረገ ጥቃት እየተናገሩ ነው ብለው ያስቡ ይሆናል። በይበልጥ ደግሞ የወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ምህጻረ ቃል (SEAH) የማይታወቅ ቃል ነው ስለ ወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ

ትንኮሳ እየተወያየህ ነው እንጂ በአጠቃላይ በማህበረሰቡ ውስጥ ስለሚደርስ ጉዳት እና ጥቃት እየተናገርጅ እንዳልሆነ ግልጽ አድርግ። ለበለጠ መረጃ እባክዎን በሥርዓተ ጾታ ተኮር ጥቃት እና ወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ መካከል ያለውን ልዩነት የሚገልጽ የRSH ወረቀት ይመልከቱ።

- ሰዎች ጥቅም ላይ ስለሚውሉ ስያሜዎች ተመሳሳይ ግንዛቤ አላቸው ብለው አያስቡ። ተመራማሪዎች እና ምርምር ተካፋዮች እንደ PSEA ወይም ወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ያሉ ምህፃረ ቃላትን ባይናገሩት እንደ እንግሊዘኛ ወይም ፈረንሳይኛ ባሉይፋዊ ወይም ዋና ቋንቋዎች ሊያውቋቸው ይችላሉ። ምንም እንኳን ሰዎች ይህን ቃል ከዚህ በፊት እንደሰሙት እና እንደሚያውቁት ቢናገሩም፣ ትርጉሙን በተመለከተ ተመሳሳይ አረዳድ እንዳላችሁ አድርገው አያስቡ። ስለ ተመሳሳይ ነገር እየተነጋገራችሁ መሆናችሁን ለማረጋገጥ ስለ ቃሉ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያብራሩ ይጠይቋቸው።
- ሰዎች ስለ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ለመናገር የበለጠ ምቾት በሚሰማቸው አውድ ውስጥ፣ አለመግባባቶችን ለማስወገድ ሲባል ትክክለኛዎቹን ቃላት መጠቀም የተሻለ ነው። ይህም በመጀመሪያ ሰዎች "በፆታዊ ብዝበዛ"፣ "ወሲባዊ ጥቃት" እና "ወሲባዊ ትንኮሳ" ሲባል የሚረዱት ምን እንደሆነ መወያየትን እና ሁሉም ሰው በኋላ ላይ ተመልሶ ሊጠቀመው በሚችለው አጭር ፍቺ ላይ ስምምነት መድረስን ሊጨምር ይችላል።
- በተመሳሳይ፣ እንደ "የወሲብ ሰራተኛ" ያሉ ድርጅትዎ አክብሮት ለማሳየት ሊጠቀምባቸው የሚችላቸው አንዳንድ ስያሜዎች፣ ለተሳታፊዎች እንግዳ ሊሆኑ ይችላሉ፣ በምትኩ "ሴተኛ አዳሪ"ን ሊጠቅሱ ይችላሉ። እንደዚህ ባሉ አጋጣሚዎች ምን ለማለት እንደፈለጉ ማብራራት እና ለቃለ መጠይቁ ዓላማ ሁሉም ሰው በሚረዳው ቃል ላይ መስማማት ሊኖርብዎ ይችላል።

**ሳጥን 3 የምርምር መሳሪያዎችን ትርጉም እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል።**

በትርጉም ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችል ግራ መጋባትን ወይም የፍቺ ልዩነቶችን ለመለየት እና የጋራ፣ ትክክለኛ ግንዛቤ መኖሩን ለማረጋገጥ የምርምር መሳሪያዎችን የአካባቢዊ ቋንቋ ትርጉም ከምርምር ረዳቶች እና ተቆጣጣሪዎቻቸው ጋር በመሆን ይፈትሹ።

የሚጠየቁ ጥያቄዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- ✓ ይህ ጥያቄ ምን ማለት ነው?
- ✓ የትኞቹ የጥያቄው ክፍሎች ግልጽ አይደሉም?
- ✓ የምርምር ተሳታፊዎች የትኞቹን ጥያቄዎች በተሳሳተ መንገድ ሊረዱ ይችላሉ?
- ✓ ከጥያቄዎቹ መካካከል ምቾት የሚነሳዎት የትኛው ነው?
- ✓ ይህን ጥያቄ ለጓደኛዎ ወይም ለቤተሰብዎ አባል ቢያቀርቡት እንዴት ብለው ይጠይቁት ነበር?
- ✓ የታሰበውን ትርጉም በተሻለ መልኩ የሚያስተላልፉ የአካባቢ ቃላት እና ሀረጎች አሉ?

መሳሪያዎቹን በመንደፍ ወይም በመተርጎም ላይ ያልተሳተፈ የስራ ባልደረባዎ የተተረጎመውን ጽሑፍ ትርጉም በቃል ወደ መጀመሪያው ቋንቋ እንዲያስተላልፍ ይጠይቁና እና ትክክል መሆኑን ያረጋግጡ። በዚህ መሠረት የዳሰሳ ጥናቱን ጥያቄዎች ዋና ትርጉም ሳይቀይሩ እርማቶችን ያድርጉ።

እንደ የመጨረሻ እርምጃ፣ የምርምር መሳሪያዎችን በታለመው ህዝብ መካከል ይሞክሩ እና መረጃ መሰብሰብ ከመጀመርዎ በፊት ማንኛውንም ማስተካከያ ያድርጉ።

## በአስተማማኝ ክትትል፣ ግምገማ እና ምርምር ላይ ተጨማሪ የመረጃ እና ድጋፍ ማዕከል መመሪያ።

- **አስተማማኝ የክትትል ጉብኝቶችን ለማካሄድ የመረጃ እና ድጋፍ ማዕከል ዋና ምክሮች**
- **የተግባራዊ ክንውን መመሪያ: ደህንነቱ የተጠበቀ እና ስነምግባር ያለው ክትትል፣ ግምገማ እና ጥናት እንዴት መንደፍ እና ማቅረብ እንደሚቻል**
- የተግባራዊ ክንውን መመሪያ እንዴት ወሲባዊ ብዝበዛ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ላይ በአስተማማኝ ሁኔታ ላይ ምርምር ማድረግ እንደሚቻል።
- **ምርምር: ደህንነቱ የተጠበቀ እናድርገው**

ይፋ የሆነ